መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
Kidst Slassie Ethiopian Orthodox Tewahido Church
P.O. Box 42204 Arlington, VA 22204 (703) 606-1976
የአገልግሎት አድራሻ፡ 5901 Leesburg pike, Falls Church, VA 22041

# ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከየት ወደ የት!
## (የ11 ዓመት የቤተ ክርስቲያኗ ጉዞ)
## መስከረም 2007 ዓ.ም.

# 1. አመሠራረት

ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዛሬ 11 ዓመት እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ቅዳሜ ግንቦት 2 ቀን 1995 ዓ.ም. በፈረንጆች አቆጣጠር ደግሞ Saturday May 2, 2003 በአሌሳንድሪያ ቨርጂኒያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና (ሥርዓት) ጠብቆ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መልካም ፈቃድ፣ ቡራኬና ጸሎት ተመሠረተች።
ቤተ ክርስቲያኗ በፍትሐ ነገሥት (ቀኖና ቤተ ክርስቲያን) መሠረት በወቅቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአሜሪካ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በነበሩት የአሁኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትረያክ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በጎ ፈቃድ፣ ቡራኬና ቅዳሴ ተመሥርታ አገልግሎቷን መስጠት ጀምራለች፡፡ የመጀመሪያ የሆነው የዕለቱ ቅዳሴ የተመራውም በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና 10 የሚሆኑ ካህናት በተገኙበት ነበር። የእለቱ አገልግሎት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለታሪክ የተቀዳ ቪዲዮ በቤተ ክርስቲያኗ የታሪክ ማህደር ይገኛል።

# 2. የመጀመሪያዎቹ 8 የአገልግሎት ዓመታት (በትንሿ ቤተ ክርስቲያን)

የመጀመሪያዎቹ ስምንት ዓመታት አገልግሎቱ ሲሰጥ የነበረው ዘወትር ቅዳሜ ስካይ ላይን ሞል በመባል ይታወቅ የነበረው በአሁኑ ሰዓት የታርጌት ገበያ ማዕከል ፊት ለፊት ባለችው ትንሿ ቤተ ክርስቲያን ነበር። በዚሁ የአገልግሎት ዘመን ከሳምንታዊው የቅዳሜው የቅዳሴ አገልግሎት በተጨማሪ ብዙ የአገልግሎት ዘርፎች የነበሩን ሲሆን ለአብነት ያህል፡

1. የእሁድ ጉባኤ
2. የማክሰኞ ጉባኤ
3. የፍኖተ ሕይወት የራዲዮ አገልግሎት....ወዘተ መጥቀስ ይቻላል።

### *ያጋጠሙን ፈተናዎች:*

የመጀመሪያዎቹ ስምንት ዓመታት ፈታኝ ዓመታት ሊባሉ ቢችሉም በተለይ የመጀመሪያዎቹ 5 ዓመታት ቤተ ክርስቲያንዋን ለማዘጋት የቃጡ ብዙ ፈተናዎች የተጋፈጥንበት ጊዜ ነበር። አጋዕዝተ ዓለም ቅድስት ሥላሴ ኃይልና ብርታት በመሆን አጽንተው የማይታለፈውን አሳልፈው ለዚህ ቀን አድርሰውናልና ክብርና ምስጋና ለፈጣሪ ለሥላሴ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይሁን እንላለን።

### *ከፈተናዎቹ በከፊል ለአብነት ያህል፡*

1. የፓርኪንግ እጦትና የምእመናንና የአገልጋዮች መኪና በየጊዜው መወሰድ (መጎተት)
2. አገልግሎቱ ቅዳሜ ብቻ በመሆኑ ቅዳሜ ብዙ ሰው ስለሚሠራ በቂ ምእመናን አለመምጣት
3. ከላይ በተገለጹት ችግሮች ምክንያት የምእመናን አለመምጣትና የቤተ ክርስቲያንዋ መሠረታዊ ወጭዎች (የቤተ ክርስቲያኑ ኪራይ፣ የካህናት አበል...) መሸፈን አለመቻል
4. የቤተ ክርስቲያንዋ ጥበት
5. በዓበይት ዓመት በዓላት በቤተ ክርስቲያንዋ ጥበት ምክንያት በዓላቱ በሌላ ቤተ ክርስቲያን ለማክበር የሚደርሰው የንዋየ ቅድሳቱ መንገላታት፣ የአገልጋዮች ድካም፣ ለኪራይ የሚወጣው ከባድ ወጪ፣ ወዘተ...

## 3. ላለፉት 3 ዓመታት አሁን ባለንበት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

- ላለፉት ሦስት ዓመታት አሁን ባለንመበት ቦታ (5901 Leesburg pike, Falls Church, VA 22041) አገልግሎቷን አጠናክራ በመቀጠል ህዝበ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ትገኛለች።
- የመጀመሪያው ዓመት በዚህ ቤተ ክርስቲያን እሁድ ብቻ ስንቀድስ የቅዳሜው አገልግሎት በተለመደው መልኩ በትንሿ ቤተ ክርስቲያን ቀጥለዋል።
- የመጀመሪያው ዓመት በዚህ ቤተ ክርስቲያን ያጋጠሙን ችግሮች፤
  - ❖ የእሁዱ አገልግሎት በአዲሱ ቤተ ክርስቲያን ማለማመድና ማስተዋወቅ፣
  - ❖ የሁለቱ ቤተ ክርስቲያን ኪራይ መክፈል፣
  - ❖ ለሁለቱ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሚሚላት
  - ❖ ለሁለቱ ቤተ ክርስቲያን መገልገያ ንዋየ ቅድሳት ሚሚላት.....ወዘተ ረገድ ሌላ ፈተና የተጋረጠብን ሲሆን አሁንም በሥላሴ ድጋፍ ተቋቁመነው አልፈናል።
- ሁለተኛው ዓመት ላይ የቅዳሜው አገልግሎትም ወደ አሁኑ ቤተ ክርስቲያን በመሳብ ህዝቡም እያወቀው በመሄዱ ነገሮች እየተቀየሩ በመምጣት ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንዋ በአስተማማኝ ሁኔታ የቆመችበት ጊዜ ነበር።
- ሦስተኛውና ያለፈው ዓመት ብዙ ህዝብ የመጣበትና አገልግሎቷም የሰፋበት መጠነኛ የአቅም ግንባታም የተደረገበት የቤተ ክርስቲያንዋ ታላቅ ዓመት ነው።

## 4. የቤተ ክርስቲያንዋ የአገልግሎት አቅም በአሁን ወቅት

ዘወትር ቅዳሜ እሁድ ከጥዋቱ 5-11am ቅዳሴው፣ ስብከተ ወንጌሉ፣ ዝማሬው...በተጠናከረ መልኩ እየቀጠለ ሲሆን በተጨማሪም፡

1. ቤተ ክርስቲያን መምጣት ለማይችሉ በፌየርፋክስ ዙሪያ በሚገኙ ከተሞች ለሚኖሩ ምእመናን "ፍኖተ ሕይወት ዘተዋህዶ" በመባል በሚታወቀው የቴሌቪዥን መርሃ ግብር እንደየ ወቅቱ ድንቅ የሆኑ ዝማሬዎች ከልጆቻቸው ጋር ፈጣሪያቸውን እንዲያመሰግኑበትና በዓላቱን በማሰብ የበረከቱ ተካፋዮች እንዲሆኑ እንዲሁ የወንጌሉን የምስራች ቃል እንዲሰሙበት ላለፉት 5 ዓመታት አሰራጭተናል አሁንም በማሰራጨት ላይ እንገኛለን።
2. በዓለም ዙሪያ ተበትነው ላሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በሙሉ በwww.1amlak.org ድረ ገጽ የተለያዩ የምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት የሚገነቡ መንፈሳዊ ዝግጅቶች በማቅረብ እንገኛለን።
3. በጸበል በኩል ስመ ሥላሴ የተጠራበት የጻድቁ አባታችን አቡነ ገብረ መንገስ ቅዱስ ገድል የተነበበበት ከበን አድራጊ ምዕመናን በመተባበር ሁሌ ማቅረብ
4. ከቤተ ክርስቲያኑ በለቤቶች ጋር በመተባበር የThanks Giving dinner በማዘጋጀት ነዳያንን ማብላት
5. VIRGINIA HOSPITAL CENTER የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በሆስፒታሉ በመገኘት መጸለይ፣ በማፅናናት...
6. ቤተ ክርስቲያንዋን የሚረከቡ ዲያቆናት ቅዳሴን ጨምሮ የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት ማስተማር
7. ከባለ ሙያዎችና በጎ ፈቃድ ካላቸው አገልጋዮች በመሆን ሕጻናት ሃይማኖታቸውና ባህላቸውን ማስተማር
8. ሐዘን የደረሰባቸው ምእመናን በግዜውም ባለ ጊዜውም በፈለጉን ጊዜ በመገኘት ማጽናናት
9. የታመሙትን በቤታቸው በመገኘት የጸሎት አገልግሎት መስጠት፤
10. የጸበል ጥምቀት መስጠት
11. የተጣሉትን ባሉበት እየሄድን ማስታረቅ
12. የምዕመናንን መንፈሳዊ ህይወት የሚገነቡ ንዋየ ቅድሳት ለምሳሌ፤

- የጸሎት መጻሕፍቶች፣
- ስዕለ አድኅኖዎች፣
- የልጆች የሃይማኖትና የቋንቋ መማሪያዎች፣
- የክርስትና ምልክት የሆነውን የአንገት መስቀል፣
- የምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት የሚገነቡ የተለያዩ የትምህርትና የዝማሬ ሲዲዎችና ዲቪዲዎች...ወዘተ በነጻ በመስጠት።

እነዚህንና የመሳሰሉትን መጠነ ሰፊ በቤተ ክርስቲያንዋ የሚሰጡ አገልግሎቶች በሙሉ ወደው ፈቅደው ከአገልግሎቱ በኋላ ከሚያቀርቡት መባ በስተቀር ያለ ምንም ክፍያ ትሰጣለች።

## 5. የቤተ ክርስቲያንዋ የወደፊት እቅድ

1. የፈጣሪያችን የሥላሴን ታቦት ከመንበሩ እንዳይነሳ፣ የተቀደሰበት ቤተ መቅደስ እንዳይፈርስ፣ ምእመናንም በፈለጉበት ጊዜ መጥተው የሚጸልዩበት ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙበት የራሳችን ቤተ መቅደስ ከ1 ዓመት እስከ 2 ዓመት ባለው ጊዜ መግዛት/መሥራት
2. ቤተ ክርስቲያኗ ብዙዎቹ ልጆችዋ በሚፈልጓት ጊዜ መድረስ ትችል ዘንድ የምትሰጠው ያለችው አገልግሎቷን ማስፋትና ማጠናከር
3. ሕዝበ ክርስቲያኑ ለሥላሴ ታቦት ማረፊያ፣ ለተቸገሩ መሸሸጊያ፣ ላዘኑ መጽናኛ፣ ለጠፉት መዳኛ፣ የሚሆን የእግዚአብሔርን ቤት በመሥራት ከበረከቱ ተካፋይ እንዲሆኑ ማበረታታት
4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ዘወትር በፀሎት መጠየቅ
5. በሀገር ቤት ያሉት ከፍተኛ የመገልገያ ንዋየ ቅድሳት ችግር ያለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ታማኝ ከሆኑት አገልጋዮችና ምእመናን በመተባበር አስተማማኝ በሆነ መንገድ መርዳት

## 6. የቤተ ክርስቲያንዋ የወደፊት እቅድ ቀጣዩን ትውልድ በመቅረጽ

### (ቤተ መቅደሱ ከሠራን በኋላ)

1) የመዋዕለ ህጻናት ትምህርት ቤት መክፈት
2) ተተኪው ትውልድ ባህሉንና ሃማኖቱን መሠረቱንም ያውቅበት ዘንድ ቤተ መጻህፍትና ቤተ መዘክር መሥራት
3) ወላጆች ልጆቻቸው ቋንቋን ለማስተማር ለሚያደርጉት ጥረት ድጋፍ ይሆን ዘንድና የሀገራችን ቋንቋ ለማወቅ ፍላቶት ላላቸው በጋብቻ፣ በሃይማኖት ወዘተ...ከሀገራችን ልጆች ጋር ለተሳሰሩ የውጭ ዜጎችም የቋንቋ ትምህርት መስጠት
4) ከዚህ ተወልደው ያደጉና የሀገራችን ቋንቋ ለማያውቁ ወጣቶችና ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለመጡት የውጭ ዜጎች በእንግዚዘኛ ሊቀድሱና ሊያስተምሩ በማስተማር ላይ ባለነው ወጣቶች የቅዳሴና የትምህርተ ወንጌል መርሃ ግብር በመጀመር ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው መሳብ።
5) ወላጅ ለሌላቸው ልጆች ከባለ ሙያዎችና  ከበጎ አድራጊዎች በመተባበር ራሳቸው የሚችሉበት የሙያ ስልጠና መስጠት

## 7. የቤተ ክርስቲያዋ አቅም በአሁኑ ሰዓት (ንዋየ ቅድሳትና ገንዘብ) as 10/10/14

- ለሁለት ቤተ ክርስቲያን ሞልቶ በመጠኑ የተረፈ ንዋየ ቅድሳት•••
- በተንቀሳቃሽ=30000
- በማይንቀሳቀስ=11000 (ለቤተ ክርስትያኑ ሥራ ቀደም ብሎ የተሰበሰብ)
- በጠቅላላ በእጅ ያለው=41000+
- ያልተሰበሰበ=20000+
- ንብረት (በንዋየ ቅድሳት)=50000+
- በጠቅላላ በንብረትና በገንዘብ=111000